ነው፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የሰራው የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የቀሪዎቹ ተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት ሟች አቶ አድነው አወቀ ሳይቃወሙ በቀሩበት ሁኔታ ሳይሆን ይልቁንም ፈቃዳቸውን ሠጥተዋል በተባለበት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ ሕጉ በወጣበት ዘመን ግለሰቦች በመሬት ባለቤትነት ረገድ መብት የነበራቸው ቢሆንም አሁን ባለው ሁኔታ ደግሞ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት መሬት በግል ባለቤትነት መያዙ ቀርቶ የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት እንዲሆን የተደረገ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች የመሬቱ ባለቤት ስለሆኑ አመልካች በመሬቱ ላይ የሰራውን ቤት የዋጋ ግምቱን ¼ኛ ከተጠሪዎች ተቀብለው ቤቱን ያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሣኔ በዚህ ረገድ ከነበረው ሕግም ሆነ ከሕገ መንግሥታችን ጋር የተጣጣመ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05950 በሕዳር 9 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 43119 በሕዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ለተጠሪዎች ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 30461

ህዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሂሩት መለሰ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ነ/ፈጁ መስፍን ታዬ

**ተጠሪ፡-** አቶ ኢሳ መሐመድ ጠበቃ ከፍያለው በላቸው

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ይህ ሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ በአመልካችና በሥር 2ኛ ተከሳሽ ላይ በኢሉባቦራ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አሸዋ አውጥቼ ለመነገድ ከዞኑ ንግድ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም መምሪያ ፈቃድ እንደዚሁም ከዞኑ የሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በመሐንዲስ ቦታው ተለክቶ ካርታ የተሰጠኝ ሲሆን ተከሳሾች ወደ ይዞታዬ ገብተው አሸዋዬን እንዳይወስዱ ብከለክላቸውም ፈቃደኛ ባለመሆን ከመጋቢት 7 ቀን 1996 እስከ መጋቢት 12 ቀን 1996 ዓ.ም. ድረስ በአራት መኪና አሸዋዬን ተመላልሰው የወሰዱብኝ ስለሆነ ጠቅላላ ዋጋውን ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ ክሱ ካስከተለው ወጭና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ክስ በማቅረባቸው ነው፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሳሽ ለክሱ ምክንያት በሆነው ቦታ ላይ የንግድ ፈቃድና ካርታ የተሰጠ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ 1ኛ ተከሳሽ /አመልካች/ አሸዋ የሚወጣበት ቦታ የእኛ ነው ከማለት በስተቀር ያቀረበው ማስረጃ ስለሌለና 2ኛ ተከሳሽም አሸዋውን መጫኑን ስላልካደ ኃላፊ ናቸው ብሎ በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍሉ በመወሰኑና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናቱ አመልካች መሠረታዊ

የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረቡ ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ታዟል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም በአመልካች በኩል የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ አመልካች ክስ በቀረበበት ጉዳይ ኃላፊ ነው ተብሎ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ከአዋጅ ቁጥር 80/89 አኳያ የሰበር አቤቱታው ሊጣራ የሚገባ ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የክርክሩ ነጥብ አመልካች ለተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለመክፈል ይገደዳል ወይ የሚለው በመሆኑ ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የሥር ፍ/ቤቶች ለውሳኔያቸው መሠረት ያደረጉት ለክርክሩ መነሻ ምክንያት በሆነው የአሸዋ ማምረቻ ቦታ ላይ ለተጠሪ ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል የንግድ ፈቃድና ካርታ የተሰጠ ስለሆኑና አመልካች በዚሁ የአሸዋ ማምረቻ ቦታ ባለመብት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያላቀረበ ስለሆነ ከተጠሪ ይዞታ ለተወሰደው አሸዋ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ለመክፈል ይገደዳል በማለት ነው፡፡

በሌላ በኩልም የአመልካች መ/ቤትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 80/89 አንቀጽ 6/18/ መሠረት ለአውራጎዳናዎች ግንባታና ጥገና እንደዚሁም ለመኖሪያ ለመሣሪያ ማሳረፊያና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶች ያለክፍያ በነጻ እንደሚጠቀምና በሚጠቀምበት መሬት ላይ ለሚገኙ ንብረቶች በሕግ መሠረት ካሳ እንደሚከፍል ተመልክቷል፡፡ የአመልካች መ/ቤትም የተቋቋመው አውራጎዳናዎችን ለማልማትና ለማስተዳደር እንደዚሁም በመንገዶች ሥራ ወጥነትን ለማረጋገጥና የመንገድ አውታር በተቀናጀ መልኩ የሚያድግበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር እንደሆነ በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 5 ላይ ተመልክቷል፡፡

አመልካች የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶች በነፃ መጠቀም እንደሚችል በተጠቀሰው አዋጅ የተፈቀደለት እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ አዋጅ በመጥቀስ በኢሉባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት



ክርክር ያቀረበ ቢሆንም በዝምታ የታለፈ ሲሆን በኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ ክርክር ሲደረግ ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ እንዳሰፈረው በይ/ባይ የተጠቀሰው ይሄው ሕግ አሸዋና ድንጋይ ሊጠቀም የሚችል መሆኑን የሚገልጽ እንጂ በይዞታነት ለሌላ ሰው በተሰጠ የአሸዋ ማምረቻ መጠቀም እንደሚችል ስለማይገልጽ ሕጉ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይሁንና የአመልካች መ/ቤት የተቋቋመበት አጠቃላይ አላማ ለሀገርና ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም መሠረት ልማትን በመላ ሀገሪቱ ለማስፋፋት እንደመሆኑ መጠን መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶችን በነፃ መጠቀም እንደሚችል በሕግ ተፈቅዶለታል፡፡

አመልካች መሬትና ድንጋይ ነክ የሆኑ ሀብቶችን በነፃ ሲጠቀም በመሬቱ ላይ የሰፈረ ንብረት ካለ ለዚሁ ንብረት ካሳ እንደሚከፍል በተጠቀሰው አ/ቁ. 80/89 አንቀጽ 6(18) ላይ ከመመልከቱ በስተቀር ለድንጋዩም ሆነ ለአሸዋው ገንዘብ መክፈል እንዳለበት አልተመለከተም፡፡

ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው መሬትም ሆነ ድንጋይ ነክ ሀብት የተፈጥሮ ሀብት እንደመሆኑ መጠን የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት ደግሞ መንግስትና ሕዝብ እንደሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ም ሆነ በክልል ሕገ መንግስታት በግልጽ የተንጸባረቀ ስለሆነ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ረገድ መንግስትና ሕዝብ ባለቤት ከመሆናቸው አኳያ በነጻ የመጠቀም መብት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው አሸዋ የሚገኝበት ቦታ የንግድ ፈቃድና ካርታ ከሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተሰጠው ቢሆንም አሸዋ የተፈጥሮ ሀብት ከመሆኑ አኳያ በዚህ የተፈጥሮ ሀብት የባለቤትነት መብት የማይኖረው ከመሆኑም በላይ በክሱም የጠየቀው አሸዋውን ለመሰብሰብ የወጣ ወጭ ሳይሆን የአሸዋውን ዋጋ ስለሆነ ይህም የሕግ መሠረት ስለሌለው የኢሉባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የአሸዋውን ዋጋ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡